ሞንትጎሜሪ ካውንቲ የጤና እና የሰብዓዊ አገልግሎት ክፍል
የግል ምስጢር ጥበቃ አሠራሮች ማስታወቂያ
አማርኛ
NOTICE OF PRIVACY PRACTICES

ይህ ማስታወቂያ የእርስዎ የጤና እና ሌላ የግል መረጃዎ እንዴት በጥቅም ላይ እንደሚውል ወይም እንዴት ለሌላ እንደሚገለጽ እንዲሁም እርስዎ ይህንን መረጃ እንዴት ለማየት እንደሚችሉ ይዘረዝራል። እባክዎ ይህንን በጥንቃቄ ይመልከቱ

አገልግሎቶቻችን እና የምንሰበስበው ማስረጃ

የሞንትጎሜሪ ካውንቲ የጤና እና የሰብዓዊ አገልግሎቶች ክፍል (ዲኤችኤችኤስ) አንድ ትልቅ የልዩ ልዩ አገልግሎት ድርጅት ሲሆን የሚሰጣቸው አገልገሎቶችም የጤና፡ የአእምሮ ጤና፡ የተከለከሉ ዕጽዋት መጠቀም፡ የልጅ ደህንነት የገቢ ድጋፍ እና ሌሎች ሕብረተሰብ አገልገሎቶች። አገልገሎቶችን ለእርስዎ ለመስጠት የዲኤችኤችኤስ ሠራተኞች ብዙ የግል መረጃዎችን ይጠይቁዎታል በመዝገብዎ ውስጥም ያስቀምጧቸዋል። ይህ መረጃ የሚከተሉትን ይጨምር ይሆናል፡

- እንደ ስምዎ፡ አድራሻ፡ የስልክ ቁጥር፡ የልደት ቀን እና ሶሻል ሴኪውሪቴ ቁጥር ያሉ ማንነትዎን የሚየረጋግጡ መረጃዎች።
- የገንዘብ መረጃ፡ ይህ መረጃ የሚያካትተው ስለ ስምዎ፡ በባንክ ያሉዎት ሂሳቦች ወይም ሌላ ሃብት እንዲሁም ያለዎትን ማናቸውንም የኢንሹራንስ ሽፋን።
- በምስጢር የሚያዝ የጤና መረጃ ስለ አለፈው ፡ ሰላሁኑ ወይም ሰለወደፊቱ የጤና ወይም አእምሮ ጤና ሕክምን የሚነግረንን ማናቸውንም መረጃ ይጨምራል።
- ስለ ጥቅሞች መረጃ ወይም እርስዎ አሁን ስለሚያገኟቸው ወይም ሰለተሰጡዎ አገልገሎቶች።

የኛ ኃላፊነቶች

የርስዎን የጤና እና ሌሎች የግል መረጃዎቸዎን ምስጢርነት የፌዴራል እና የእስቴት ሕጎች ይጠብቃሉ እኛም እነዚያን ሁሉ ሕጎች አክብረን እንከተላለን። መረጃዎን በደህና ሁኔታ ጠብቀን ለማስቀመጥ ተገቢ እርምጃዎችን እንወስዳለን፡ መረጃዎን እንጠቀምበታለን (በዲኤችኤችኤስ ውስጥ እናጋራለን) እንዲሁም ለሌላ እንገልጻለን (ከዲኤችኤችኤስ ውጭ እናጋራለን) ይህንንም የምናደርገው ሥራችንን ለማከናወን አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ እና በሕግ በተፈቀደ ወይም በታዘዘ ጊዜ ብቻ ይሆናል።

ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት በስተቀር በሌላ ምክንያት የርስዎን መረጃ እኛ መጠቀም ወይም ለሌላ መግለጽ ካስፈለገን፡ የእርስዎን የጸሑፍ ፈቃድ እንጠይቃለን። የሰጡንን ማናቸውንም የጽሑፍ ፈቃድ የመሰረዝ መብት አለዎ። የሰጡትን ፈቃድ ከሰረዙ፡ የሰጡንን ፈቃድ መሠረት በማድረግ ቀደም ሲል ያደረግነውን የመረጃዎ መጠቀም ወይም መግለጽ አይመለከትም።

ይህንን *የግል ምስጠር ጥበቃ አሠራሮች ማስታወቂያ* እንድንሰጥዎ እና ተከታትለን እንድንፈጽም ሕግ ያስገድደናል። የዚህን *ማስታወቂያ* አንቀጾች እና የግል ምስጠር ጥበቃ አሠራሮችንን ለመለወጥ እና ይህም ለውጥ አኛ ዘንድ ባስቀመጥናቸው የጤና እና ሌሎች የግል መረጃዎች ላይ ሁሉ ተፈጻሚ ለማድረግ መብት አለን። በሚቀጥለው ቢሮአችንን በሚጎበኙበት ጊዜ በግል ምስጢር ጥበቃ አሠራሮችን ላይ ስለተደረጉ ማናቸውም ለውጦች እናሳውቅዎታለን። ወቅታዊው ማስታወቂያችን በእንግዳ ማረፊያ ክፍሎቻችን እና በዲኤችኤችኤስ ድረ ገጽ ላይ በwww.montgomerycountymd.gov ይገኛል።

እንዴት ያለ እርስዎ የጽሑፍ ፈቃድ መረጃ እንደምንጠቀም ወይም ለሌላ እንደምንገልጽ

- **ለሕክምና እና አገልገሎቶች፡**
  ከርስዎ ጋር የሚሠሩ የዲኤችኤችኤስ ሠራተኞች ለእርስዎ የተቀነባበረ ሕክምና እና አገልገሎቶች ለመስጠት የእርስዎን የጤና እና ሌሎች የግል መረጃዎች ይጠቀሙባቸው ይሆናል። ምሳሌዎች፡

- ከክሊኒኮቻችን ውስጥ ባንዱ የጤና እንክብካቤ የሚያገኙ እና ለሌላ እንደ መኖሪያ ቤት እርዳታ ወይም የገቢ ድጋፍ ለማግኘት ለማመልከት ከፈለጉ፡ የርስዎን ጉዳይ የያዙት ሠራተኛ ወደ ሌላ በመምራት እና የብቁነት መረጃን በመጋራት እነዚህን አገልግሎቶች እንዲያገኙ ይረዱዎት ይሆናል።
- ከአንድ በላይ የዲኤችኤችኤስ አገልግሎት የሚቀበሉ ከሆኑ፡ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ አንድ የተቀነባበረ ዕቅድ ለማውጣት የእርስዎን ጉዳይ የያዙት ሠራተኞች እርስ በርሳቸው ለመነጋገር ይችላሉ።

በሚከተሉት ፕሮግራሞች የሚሠሩ የዲኤችኤችኤስ ሠራተኞች ያለ እርስዎ ፈቃድ የፕሮግራም መረጃዎችን በሌሎች ፕሮግራሞች አገልግሎት ለሚሰጡዎ ሠራተኞች ለማካፈል አይችሉም።

- አልኮል እና የተከለከሉ ዕጽዋት ያላግባብ መጠቀም ሕክምና
- የቤት ውስጥ በደል፡ የግብረ ሥጋ ጥቃት ወይም የወንጀል ሰላባ እርዳታ ፕሮግራሞች
- በ1974 የቤተሰብ የትምህርት መብቶች እና ምሥጢርነት ሕግ "የትምህርት ማስረጃዎች" የተባሉ ማስረጃዎችን የሚያስቀምጡ የዲኤችኤችኤስ ፕሮግራሞች

የዲኤችኤችኤስ ሠራተኞች የእርስዎን መረጃ ለሕክምና እና ለአገልግሎት ከዲኤችኤችኤስ ድርጅቶቻችን ውጭ ከሌሎች ሰዎች ጋር የሚጋሩት በእርስዎ የጽሑፍ ፈቃድ ወይም በፌዴራል ወይም በእስቴት ሕግ በተፈቀደው መሠረት ይሆናል። ለምሳሌ፡የጤና እንክብካቤ የሚያደርጉልዎ የኛ የዲኤችኤችኤስ ሠራተኞች የእርስዎን የጤና መረጃ ሕክምና እያደረጉልዎ ላሉ የውጭ የጤና ተንከባካቢዎች እንዲያጋሩ የፌዴራል እና የእስቴት ሕግ ይፈቅዳል።

- **ለክፍያ፡** ለተደረገልዎ የጤና ወይም የአእምሮ ጤና አገልግሎቶች ክፍያ ለመቀበል እንዳስፈላጊነቱ የእርስዎን የጤና ወይም የግል መረጃ እንጠቀምበት ወይም እንጋራ ይሆናል። ለምሳሌ፡ ለተደረገልዎ ሕክምና ከሜዲኬድ ወይም ከሜዲኬር ክፍያ ለመጠየቅ መረጃዎን እንጠቀም ይሆናል።

- **ለጤና እንክብካበቤ/የሥራ እንቅስቃሴዎች** የእኛን ፕሮግራሞች እና እንቅስቃሴዎች ለማስተዳደር የእርስዎን የጤና ወይም የግል መረጃ እንጠቀምበት ወይም ለሌላ እንገልጽ ይሆናል። ለምሳሌ፡ በክፍሉ በኩል የሚያገኙትን የአገልግሎት ጥራት ለመመርመር ጉዳይዎን መዝገብ የዲኤችኤችኤስ ሠራተኞች ወይም የውጭ ኦዲተሮች ይመለከቱ ይሆናል።

- **ለቀጠሮዎች ወይም ለማስታዎቂያዎች፡** ቀጠሮ ለመያዝ ወይም ስለ ቀጠሮ ለማስታወስ፡ ወረቀት ጽሑፎችን ለማጠናቀቅ፡ ሊፈልጓችው ስለሚችሉ ስለሌሎች የተዛመዱ አገልግሎቶች ጥቅሞች ወይም አገልግሎቶች ለማስታወቅ ወይም በድንገተኛ አደጋ ጊዜ ለመገናኘት ከእርስዎ ወይም ከተወካይዎ ጋር እንገናኝ ይሆናል።

- **የሥራ ተባባሪዎቻችን፡** እንደ የገንዘብ ሂሳብ ወይም የሕግ አገልግሎቶች፡ ዘገባ ትንተና፡ እና ችሎታ መረጋገጥን እንዲሁም የአገልግሎት ጥራት ማረጋገጫ ምርመራን ያሉ የአስተዳደር እና የድጋፍ አገልግሎቶች ከሚያቀርቡ ከዲኤችኤችኤስ ውጭ ከሆኑ ሰዎች ጋር ስምምነቶች አሉን። እነዚህ ሰዎች የሥራ ተባባሪዎች ተብለው ይጠራሉ። እነዚህን አገልግሎቶች ለእርስዎ እንዲሰጡዎ የእርስዎን መረጃ ለሥራ ተባባሪዎች እንገልጽ ይሆናል። ሆኖም የሥራ ተባባሪዎች የእርስዎን መረጃ በጥብቅ ምስጢርነት እንዲይዙ እናዝዛቸዋለን።

- **የእርስዎ ቤተሰብ፡ ጓደኞች እና በእርስዎ እንክብካቤ የሚሳተፉ ሌሎች** የርስዎን መረጃ ለእርስዎ ቤተሰብ፡ እና በእርስዎ እንክብካቤ የሚሳተፉ ሌሎች እንገልጽ ይሆናል። ለምሳሌ፡ የቤት ውስጥ እንክብካቤን ከሚያ/ምታ/ዘጋጅ አካለ መጠን ለደረሰ/ሰች ልጅዎ ጋር ስለ የሕመምዎ ሁኔታ እንወያይ ይሆናል። ይህንን መረጃ ከቤተሰብዎ ጋር እንዳንጋራ ከፈለጉ፡ ይህን ሊጠይቁ ይችላሉ እኛም አናደርግም። እርስዎ በጽሑፍ ፈቃድ ካልሰጡን በስተቀር፡ ሰለ አእምሮ ጤናዎ ወይም ስለ ተከለከለ ዕፀጽት አላግባብ መጠቀም ታሪክዎ፡ ወይም በቤተሰብዎ ስለሚደረገልዎ እንክብካቤ የእርስዎን መረጃ አንጋራም።

- **ለመንግሥት ፕሮግራሞች፡** እንደ ሶሻል ሴኪውሪቲ ጥቅሞች ካሉ ሌሎች የመንግሥት ፕሮግራም ጥቅሞች ብቁ እንደሆኑ ለማጣራት፡ የርስዎን የጤና እና ሌሎች የግል መረጃዎች እንገልጽ ይሆናል።

- **ለሕዝብ ጤና ጥበቃ ተግባሮች፡** ለሕዝብ ጤና ጥበቃ ተግባሮች የርስዎን የጤና መረጃ እንጠቀምበት ወይም ለሌላ እንገልጽ ይሆናል። ለምሳሌ፡ ለተላላፊ በሽታ ተጋልጠው ከሆኑ (በግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚተላለፍ በሽታ)፡ ይህንኑ ለእስቴቱ እንገልጽ ይሆናል እንዲሁም የዚህን በሽታ ስርጭት ለመከላከል ሌሎች እርምጃዎችንም እንወስድ ይሆናል።

- **ስለ በደል እና ችላ ስለ ማለት ማስታዎቅ እና ምርመራዎች፡** በልጆች ላይ እና በአዋቂ ላይም እንደ ልጅ ተፈጽሟል ተብሎ ስለሚጠረጠር በደል እና ችላ ማለት መግለጽና ማስታወቅ እንዳለብን ሕግ ያስገድደናል።

- **ጉዳትን ለማስወገድ፡** ዲኤችኤችኤስ በአንዳንድ ሁኔታዎች ስለ እርስዎ የጤና ወይም ሌላ የግል መረጃ ለሕግ አስከባሪ ይገልጽ ይሆናል። ለምሳሌ፡ ከሠራተኞቻችን መካከል ባንዱ ላይ ወይም በሌላ ደምበኛ ላይ ጉዳት ካደረሱ ወይም በንብረታችን ላይ ጉዳት ካደረሱ ወይም ባለሙያ ሠራተኞቻችን እርስዎ በሌሎች ሰዎች ወይም በራስዎ ላይ ከበድ ጉዳት ያደርሳሉ ብለው ካመኑ፡ ለሕግ አስከባሪ እናስታውቃለን። እንዲሁም ዲኤችኤችኤስ እንደ የአሸባሪ ጥቃት ወይም ድንገተኛ ደራሽ ከፈተኛ አደጋ ባለ አጋጠሚ ጊዜ የርስዎን የጤና ወይም ሌላ የግል መረጃ ይገልጽ ይሆናል።

- **ለሬሳ መርማሪዎች፡ የመቃብር ቤት ዲሬክተሮች፡ የሞትን ምክንያት መርማሪዎች እና የአካል መስጠት።** ዲኤችኤችኤስ ሞትን የሚመለከት የጤና መረጃ ለሬሳ መርማሪዎች፡ የመቃብር ቤት ዲሬክተሮች፡ እና እንዲሁም የአካል ክፍል፡ ዓይን ሥጋ መስጠት ወይም ለመተካት ለተፈቀደላቸው ድርጅቶች ይገልጽ ይሆናል።

- **ለምርምር ተግባር፡** ባንዳንድ ሁኔታዎች ለሕክምና ምርምር ጥናት የርስዎን የጤና መረጃ እንጠቀምበት ወይም እንገልጽ ይሆናል። ላንድንድ ጉዳዮች፡ የርስዎ የጽሑፍ ፈቃድ ይፈለጋል። የምርምር ጥናቶች እና መግለጫዎች ሰዎችን በስም ለይተው አይገልጹም።

- **ለፍርድ ቤት ክርክሮች፡** በሕግ ወይም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ለፍርድ ቤቱ ስለ እርስዎ መረጃ እንድናቀርብ እንታዘዝ ይሆናል።

- **ሕግ በሚያዝዘው መሠረት፡** የርስዎን የጤና ወይም ሌላ የግል መረጃ እንድንገልጽ አንድ ሕግ ወይም ደንብ የሚያዝዘን ከሆነ ይህንኑ መፈጸም አለብን።

የአልኮል ወይም የተከለከለ ዕፀጽት አላግባብ መጠቀም ፕሮግራም መረጃ እንዴት እንደምንጠቀም ወይም እንደምንገልጽ

የአልኮል ወይም የተከለከለ ዕፀጽት አላግባብ መጠቀም ሕክምና መረጃ በምሥጢር መያዝ በፌዴራል ሕግ እና ደንቦች የተጠበቀ ነው። ከታች በመለከቱት ካልሆነ በቀር በአጠቃላይ፡ ከአልኮል ወይም ከተከለከለ ዕፀጽት አላግባብ መጠቀም ሕክምና ጋር የተዛመደ የእርስዎን መረጃ አንጠቀምም ወይም አንገልጽም።

- የጽሑፍ ፈቃድዎን ከሰጡን
- መግለጹ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ከተፈቀደ
- መግለጹ የሚደረገው በአደገኛ ድንገተኛ ሕመም ወቅት ለሕክምና ሠራተኞች ወይምምርምር ለማካሄድ ችሎታው ላላቸው ሠራተኞች፡ ለኦዲት ወይም ለፕሮግራም ግምገማ።

የእርስዎን መረጃ የሚመለከቱ መብቶችዎ

የሚከተሉት መብቶች አሉዎት፡

- የግል ምስጠር ጥበቃ አሠራሮች ማስታወቂያ አንድ ቅጂ የማግኘት። ጥያቄ ሲቀርብ ይህ ማስታወቂያ በተለያየ ቅርጽ ይቀርባል።
- ሁልጊዜ ከምንገናኝበት ይልቅ ሌላ ሥፍራ እንድንናገኝዎ ወይም ሌላ ዘዴ በመጠቀም እርስዎ ጋር እንድንገናኝ እኛን ለመጠየቅ። ለምሳሌ፡ ከቤትዎ መጥተን ከመገናኘት ይልቅ በስልክ ወይም በደብዳቤ እንድንገናኝዎ ሊጠይቁ ይችላሉ።
- ስለ እርስዎ ያስቀመጥነውን መረጃ ማየት፡ መመርመርና ቅጂ ማግኘት። *ይህንን ጥያቄ በጽሑፍ ማቅረብ አለብዎ፡ የመረጃዎን ቅጂ ለማዘጋጀት ለሚያስፈልገው ወጭ ክፍያ እንዲያደርጉ ይጠየቁ*

ይሆናል። መረጃዎን ለመመርመር ወይም ቅጂ ለማግኘት መብትዎን የማንሰጥባቸው አንዳንድ ሁኔታዎች አሉ። ይህ ከሆነ፡ ለምን ይህንን ውሳኔ እንዳደረግን እንገልጻለን እንዲሁም እምቢታው እንደገና እንዲመረመርልዎ እንዴት እንደሚጠይቁ ወይም እንዴት የአቤቱታ ፋይል እንደሚከፍቱ።

- እኛ ያስቀመጥነው መረጃ የተሳሳተ ወይም ያልተሟላ ነው የሚል ስሜት ካለዎ፡ መረጃዎ እንዲሻሻል (እንዲለወጥ) ጥያቄ ማቅረብ። *ይህንን ጥያቄ በጽሑፍ ማቅረብ አለብዎ*። በአንዳንድ ሁኔታዎች ለውጡን እንድናደርግ አንገደድም። ለውጡን ለማድረግ ካልተስማማን፡ ለምን እንደሆነ እንገልጻለን እንዲሁም ከኛ እንቢታ ጋር ባለመስማማት የጻሑፍ መግለጫ ለኛ ለመስጠት ስላለዎ መብት እንገልጽልዎታለን።
- ከኤፕሪል 14/2003 ወዲህ የእርስዎን መረጃ ስላደረግነው ዝርዝር መግለጫ ማግኘት (አንድ ግልጽ ዝርዝር)። ይህ መግለጫ ለሕክምና፡ ለክፍያ ወይም ለጤና እንክብካቤ ዓላማ ለሌላ መግለጽ ወይም በእርስዎ ፈቅደውልን ያደረግነውን ለሌላ መግለጽ አይጨምርም። *ይህንን ጥያቄ በጽሑፍ ማቅረብ አለብዎ*።
- የርስዎን መረጃ ለእርስዎ ቤተሰብ፡ እና ለሌሎች በእርስዎ እንክብካቤ ለሚሳተፉ ሰዎች እንዳንጋራ ጥያቄ ማቀረብ።
- የጤና መረጃዎን ለሕክምና/አገልግሎት፡ ለክፍያ ወይም ለጤና እንክብካቤ ተግባር ዓላማ እንዳንጠቀምበት ወይም ለሌላ እንዳንገልጽ ጥያቄ ማቀረብ። *እነዚህ ጥያቄዎች በጽሑፍ መቅረብ አለባቸው*። ለነዚህ ጥያቄዎች ተስማምተን እንደንፈጽም አንገደድም፡ ከተስማማን ግን፡ ለእርስዎ ድንገተኛ አደጋ ሕክምና መረጃውን መግለጽ ካላስፈለገን በስተቀር፡ስምምነቱን አክብረን መፈጸም አለብን። ጥያቄዎን ለመቀበልና ለመፈጸም ካልቻልን ለምን እንደሆነ እንገልጻለን።
- የአቤቱታ ክስ ፋይል ለመክፈት ወይም አንደ ችግርን ለማስታወቅ።

ጥያቄ እንዴት እንደሚቀርብ

ስለ እኛ የግል ምስጢር ጥበቃ አሠራሮች ጥያቄ ካለዎ ወይም ከላይ ከተዘረዘሩት ውስጥ ማንኛውንም ከፈለጉ ከእርስዎ ጋር ከሚሠሩት ሠራተኛ ጋር ይገናኙ፡ ወይም በዚህ ማስታወቂያ መጨረሻ ላይ አድራሻቸው ከተዘረዘረው የኛ የምሥጢርነት ባለሥልጣን ጋር ይገናኙ። በጽሑፍ መቅረብ ስላለባቸው ጥያቄዎች የዲኤችኤችኤስ የደምበኞች ጥያቄ ማቅረቢያ ቅጽ እንዲጠቀሙ እንጠይቃለን። ጥያቄ ማቅረቢያውን ቅጽ ከማናቸውም የዲኤችኤችኤስ ቢሮ ወይም የእኛ የምሥጢርነት ባለሥልጣን በመጠየቅ ለማግኘት ይችላሉ።

የክስ አቤቱታ ለማቅረብ ወይም ችግርን ለመግለጽ

እኛ የርስዎን መረጃ እንዴት እንደተጠቅምንበት ወይም ለሌላ ስለ ገለጽንበት የክስ አቤቱታ ለማቅረብ ወይም ችግርን ለመግለጽ እኛ የምሥጢርነት ባለሥልጣን በሚከተለው አድራሻ ያነጋግሩ።

Privacy Officer
Montgomery County Department of Health and Human Services
401 Hungerford Drive
Rockville, MD 20850
240-777-3050 (Voice) 240-777-1398 (TTY)

የክስ አቤቱታ በማቅረብዎ ወይም ችግርን በመግለጽዎ ወይም በሚደረግ ምርመራ ላይ ትብብርን በማሳየትዎ አንዳችም ተቃራኒ እርምጃ አንወስድብዎትም እንዲሁም የሚያገኟው ጥቅሞች እና አገልግሎቶች በማናቸውም መንገድ ለውጥ አይደረግባቸውም።

የክስ አቤቱታዎ ወይም ቅሬታዎ የእርስዎን የጤና መረጃ እንዴት እንደተጠቀምን ወይም ለሌላ እንደገለጽን ከሆነ፡ ከሚከተለው ጋርም መገናኘት ይችላሉ።

Region III, Office for Civil Rights, U.S. Department of Health and Human Services
150 S. Independence Mall West, Suite 372
Public Ledger Building, Philadelphia, PA 19106-9111
215-861-4441 (voice) 215-861-4441 (TDD) 1-800 368-1019 (Hotline)